# እግዚአብሔር ሆይ

እግዚአብሔር ሆይ ወሮታህ ብዙ ነው
ለጠራህ ሰው ሁሉ የእጅህን ሰጠኸው
በብዙ በረከት ህይወቱን ዳሰስከው
እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ፍቅርህ የበዛ ነው (፪)

ለድንግል ሰጠሃት ንፁህ የሆነ ልብ
ለዳዊት ሰጠኸው የበገናን ምስጢር
ለያሬድ ሰጠኸው የማህሌት ጥበብ
ታዲያ ለዚህ ሁሉ ምን ይከፈልሃል
ስጦታህን ሳስብ ልቤ ይገረማል (፪)

እዝ...

በኃጢአት ስንኖር አመፀኛ ሆነን
ልዩ የሆነውን ፍቅርህን አቃልለን
አንተ ግን ኃጢአቱን ፈፅመህ እረስተህ
የምድርን በረከት ሳትሳሳ ሰጥተህ
አመፀኛውን ሰው ታስደስተዋለህ (፪)

እዝ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org